
# ወርሓዊ ዜና ሚቲዎሮሎጂ

## Monthly Met. News






**የዓለም የሚቲዎሮሎጂ ቀን በዓል ሲከበር**

## ቅጽ 4 ቁጥር 10 የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

# የዓለም የሚቲዎሮሎጂ ቀን በዓል
# ‹‹ለአየር ሁኔታ-ዝግጁነት፣ ለአየር ጠባይ-ስልታዊ ተጠቃሚነት››
# በሚል መሪ ቃል ተከበረ

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ67ኛ ጊዜ በአገራችን ደግሞ ለ37ኛ ጊዜ **‹‹ለአየር ሁኔታ-ዝግጁነት፣ ለአየር ጠባይ-ስልታዊ ተጠቃሚነት››** በሚል መሪ ቃል መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም በራስ ሆቴል -አዲስ አበባ የዓለም የሚቲዎሮሎጂ ቀንን ሁሉም ሠራተኞችና ተጋባዥ እንግዶች በተገኙነት ማክበሩ ተገለጸ፡፡

በዓሉን በንግግር የከፈቱት አቶ ዱላ ሻንቆ የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እንዳሉት፣ ‹‹ይህ በዓል በሀገራችን የሚከበረው ለ37ኛ ጊዜ ቢሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰብ ቀደምት ታሪክ ያለውና ለበርካታ ዓመታት የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በመሰብሰብ ከ1898 ዓ.ም ጀምሮ የመረጃዎች ምዝገባ እንደተጀመረ ታሪክ ያረጋግጣል። እነዚህ መረጃዎች ለተለያዩ አገልግሎቶች ከመዋላቸውም በላይ ለሀገራችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ናቸው›› ብለዋል። አቶ ዱላ አያይዘውም፣

‹‹የዘንድሮው የዓለም የሚቲዎሮሎጂ ቀን መሪ ቃል በግልጽ እንደሚያመለክተው፣ **‹‹ለአየር ሁኔታ-ዝግጁነት፣ ለአየር ጠባይ-ስልታዊ ተጠቃሚነት››** የሚል ሲሆን ዋነኛ ትኩረቱም የዓለም ሕዝብ በርካታ የተፈጥሮ ጥፋቶች እንደተጋረጡበትና ከእነዚህም ውስጥ ማዕበላዊ ነውጦች፣ ከባድ ጎርፍ የሚያስከትል ዝናብ፣ ድርቅና ሰደድ እሳት እንዲሁም ሌሎች በርካቶች የሚገኙባቸው ሲሆን ከዚህ የተነሣም ራሳችንን ለአየር ሁኔታ ዝግጁ እንድናደርግና ለአየር ጠባይም ስልታዊ ተጠቃሚ እንድንሆን አጽንዖት የሚሰጥ ነው፡፡ በተጨማሪም አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን ያልተከተለ አካሄድም በርካታ ሰው-ሠራሽ ችግሮን አስከትሎ ለከፋ ጉዳት እያጋለጠን መሆኑንም ይጠቁማል፡፡

‹‹ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከመሠረታዊ ተልዕኮው ማለትም የሚቲዎሮሎጂ እና ተዛማጅ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተን፣ የአየር ሁኔታን፣ የአየር ጠባይ፣ የአየር ጠባይ ለውጥና የከባቢ አየር ብክለት በመከታተል እና በመተንበይ ለአገሪቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንቅስቃሴዎች ለሕይወትና ንብረት ከአደጋ መጠበቅ እገዛ የሚያደርግ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መስጠት፣ በሚለው መርሑ አስፈላጊ የሆነውን መረጃ የመሰብሰብ፣ ምርምሮችን የማድረግ እና የአየር ጠባይና ሁኔታ ግንዛቤን ለማሳደግ ተጨባጭ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከአየር ሁኔታ፣ ከአየር ጠባይ እና ከውኃ ጋር ከተያያዙ የተፈጥሮ አደጋዎች ለመታደግ ቅድሚያ ሰጥቶም ይንቀሳቀሳል፡፡ ኤጀንሲው የሀገራችን አጀንዳ የሆነውን ዘላቂ ዕድገት፣ የአየር ጠባይ ለውጥን መቋቋምንና የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለመደገፍ በጽናት እየሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህም በላይ ዕለታዊውን የአየር ሁኔታ ከመተንበይ አንሥቶ እስከ ረጅም ጊዜ የአየር ጠባይ ትንበያ የሚደርስና ኅብረተሰቡ

ለአየር ሁኔታ ዝግጁ እና ለአየር ጠባይ ስልታዊ ተጠቃሚነቱ እንዲረጋጥ በመሥራት ላይ ይገኛል›› ብለዋል፡፡ ምክትል ዋናው ዳይሬክተር ንግግራቸውን ሲያጠቃልሉም፣

‹‹ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ አሳሳቢ እየሆነ በመጣው የአየር ለውጥ ላይ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ ወስዶ ለትግበራ እንዲነሣሣ አበክሮ በማሳሰብ ላይ ይገኛል። የዓየር ለውጥ ሁላችንንም የሚመለከትና በሁሉም የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ላይ ተጽዕኖውን የሚያሳርፍ ነው። ከግብርና እስከ ቱሪዝም፣ ለመሠረተ-ልማት ግንባታ እስከ እስከ ጤና፣ ከበረራ እስከ ውኃ ልማት ድረስ ተጽዕኖ አለው። በተጨማሪም ተጽዕኖው ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር ቀጥታ ትስስር ያላቸውን ማለትም፡- ውኃ፣ ምግብ፣ እና የኃይል አቅርቦትንም ይነካል። ኤጀንሲያችንም አገራችን በማኅበረ-ኢኮኖሚው ዘርፍ የወጠነችውን የልማት ዕቅዶች እንዲሳኩና ዘላቂነታቸውም እንዲረጋገጥ በየጊዜው ዘርፉን ለማጠናከርና አገልግሎቱን ለማሻሻል በርካታ ሥራዎችን በማከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን ይሄንንም አጠናክሮ ይቀጥላል›› ብለዋል፡፡

ለዕለቱ በተያዘው መርሐ-ግብር መሠረት የዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት ዋና ፀሐፊ የፕሮፌሰር ፒተሪ ታላስ የቪዲዮ መልዕክት ለበዓሉ ታዳሚዎች ቀርቧል፡፡ ዋና ጸሐፊው በመልእክታቸው የዓመቱን መሪ ቃል ካስተዋወቁ በኋላ ባለፈው ዓመት የነበረውን ተያያዥ ችግሮች ሲያብራሩ፣ ‹‹የካርቦን ዳይኦክሳይድ ልቀት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱ፣ የዓለም ሙቀት መጠን በጣም መጨመሩና ተጠናክሮ መቀጠሉን ጠቅሰው ይህ የዓየር ጠባይ መለዋወጥም በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለአብነትም ባለፈው ዓመት በአሜሪካና በካሬቢያን የተከሰተው ማዕበላዊ ነውጥ /ሄሪኬይን/ እስከ 215 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጉዳት ማስከተሉን አመልክተው በአጠቃላይ በመላው ዓለምም 300 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጉዳት ማስከተሉን ገልጸዋል፡፡ ይኸም በተለይ በውኃና ምግብ አቅርቦት ላይ እጥረት ያስከተለ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ የዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅትም ሆነ የየአገራቱ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተቋማት ከባለ ድርሻና ተባባሪ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠሩ ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተለይተው የተቀመጡት የልማት ዕቅዶች ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር የተያያዙ መሆናቸው ዛሬ ግንዛቤ መያዙን አመላካች ሲሆን በዚህ ረገድም የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ጥረቱ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ዋና ጸሐፊው በአጽንዖት አሳስበዋል፡፡

ለዕለቱ በተያዘው መርሐ-ግብር መሠረት ሁለት የጥናት ጽሑፎች በአቶ ካሳ ፍቃዱ የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እና በአቶ አሳምነው------- የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል፡፡

በአገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሚለዋወጠው የአየር ሁኔታ ጠባይ ጋር ተያይዞ በወቅቶች ዝናብ አገባብና አወጣጥ ላይ የመዋዠቅ ሁኔታ፣ የደረቅ ሰሞንነት መደጋገም፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከባድ ዝናብ የመዝነብና ወደ ጎርፍ የመለወጥ ሁኔታ እየተስተዋለ መሆኑንም ኤጀንሲው ገልጿል፡፡

ኤጀንሲው በመንግስትና በህዝብ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ሀገራዊና ውጫዊ የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃዎችን በቅርበት በመከታተል፣ በመቃኘትና በመተንተን ለአገሪቱ ማህበራዊ ልማትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ብሎም ለህይወትና ንብረት ከአደጋ መጠበቅ እገዛ የሚያደርግ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ለመስጠት በመንግስት ከሚመደብለት በጀት በተጨማሪ ከለጋሽ ድርጅቶችና ተባባሪ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመስራቱ አሁን ላይ የማስፈፀም አቅሙ እያደገ መምጣቱ ተገልጿል፡፡

ለዚህም ማሳያው ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት እንደ አገር በኤጀንሲው ሲሰጡ የነበሩና ለመንግስት መካከለኛ ዕቅድ ዝግጅት ወሳኝ የሆኑትን የወቅት ትንበያዎችን እንኳን  ብንወስድ ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመቋቋምና ምቹ ሁኔታዎችን አሟጦ መጠቀም እንዲቻል ከአራት ወር በፊት አስቀድሞ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎቶችን በመስጠት በኩል ውጤታማ ስራዎች ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በቀጣይም ኤጀንሲው አገልግሎቱን ለማሻሻል፣ ተደራሽነቱን ለማሳደግና ከዚህ ጎን ለጎን በመረጃው አጠቃቀም ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ እንደዚህ አይነት በዓላትንም ጨምሮ በተለያዩ አጋጣሚዎች በመጠቀም ጠንክሮ እንደሚሰራ በዚህ አጋጣሚ ተገልጿል፡፡

ይህ በዓል በዓለም የሚቲዎሮሎጂ ድርጅት (WMO) አባል ሀገሮች እና ጀኔቭ ስዊዘርላንድ በሚገኘው የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት እንዲሁም በአገራችን በአስራ አንዱም የሚቲዎሮሎጂ የአገልግሎት ማዕከላት በድምቀት የተከበረ ሲሆን በበዓሉም ላይ በጡረታ የተገለሉ የቀድሞ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በሰጡት አስተያየት ኤጀንሲው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደረገ ያለውን መሻሻል አድንቀው በቀጣይም ተጠናክሮ እንዲወጣ አደራቸውን አስቀምጠዋል፡፡





## ከአየር ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ ባለ ድርሻ አካላት ጋር የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ወጪ መሸፈን ሥርዓት ዐውደ-ጥናት ተካሄደ

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከአየር ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ ባለ ድርሻ አካላት ጋር በሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የወጪ መሸፈን ሥርዓት (Cost Recovery) የሚያተኩር ዐውደ-ጥናት በፍሬንድሽፕ ሆቴል አዲስ አበባ መጋቢት 25 ቀን 2010 ዓ.ም አካሄደ፡፡

አቶ ፈጠነ ተሾመ የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር በዐውደ-ጥናቱ መክፈቻ ላይ ባደረጉት አጭር ገለጻ ጥሪውን አክብረው የተገኙትን አመስግነዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ዐውደ-ጥናትም የተዘጋጀበት ዋና ዓላማ በአየር ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ ተሳታፊ ከሆኑት ባለ ድርሻ አካላት ጋር ስለ ወጪ መሸፈን ሥርዓት ኤጀንሲው አጥንቶ ባቀረበው ጽሑፍ ላይ መወያየት መሆኑን በአጽንዖት ገልጸው፣ ሰነዱን ለማዳበር ጠቃሚ ሐሳቦች እንደሚገኙ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል፡፡

አቶ ካሣ ፍቃዱ የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርና የዐውደ-ጥናቱ አስተባባሪ እንግዶቹን አመስግነው የዕለቱን መርሐ-ግብር አስተዋውቀዋል፡፡

ለዕለቱ በተያዘው ፕሮግራም መሠረት፣ ‹‹የወጪ መሸፈን ሥርዓት መርሖዎችና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች›› በሚል ርዕስ የመጀመሪያው የጥናት ጽሑፍ በአቶ ዮሴፍ ውብታዬ የሚቲዎሮሎጂ መሣርያዎችና ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ቀርቧል፡፡ በይዘቱም ከተለያዩ አገሮችና ተቋማት የተገኙትን ተሞክሮዎች አቅርበዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የቀረበው የጥናት ጽሑፍ፣ ‹‹የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲ ጥናት›› የሚል ሲሆን አቅራቢውም አቶ ክንፈ ኃ/ማርያም የጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ናቸው፡፡ አቶ ክንፈ የፖሊሲ ጥናቱ ማሳያ ምሳሌዎችን በመንተራስ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት አሰጣጥም የሀገሪቱን ሕግጋትና ዓለም አቀፍ የአሠራር መርሖዎችን ተከትሎ የተነደፈ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ እስካሁን ባለው ሁኔታም ኤጀንሲው ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ዋጋ እንደማያገኝ ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻ የቀረበው የጥናት ጽሑፍ፣ ‹‹የወጪ መሸፈን ሥርዓት የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት የዋጋ ታሪፍ›› የሚል ሲሆን አቅራቢውም አቶ ታፈሰ ረጋሳ የትምህርትና ሥልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ናቸው፡፡ አቶ ታፈሰ በገለጻቸው ታሪፉ የወጣበትን ታሳቢ ተመን አማራጮች በዝርዝር አቅርበው ይህም

እስካሁን ከሚሰበሰበው ገቢ ከ500 ሺህ ብር ወደ 35.5 ሚሊዮን ብር እንደሚያድግ አመልክተዋል፡፡ ለዚህም ይሆን ዘንድ የታንዛንያን ተሞክሮ መቃኘቱን ገልጸዋል፡፡

ሦስቱም የጥናት ጽሑፎች ቀርበው ሰፊ ውይይት የተካሄደ ሲሆን ተሳታፊዎችም የአየር ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ ከሚቲዎሮሎጂ መረጃ ጋር በእጅጉን የተቆራኘ ሲሆን የአገልግሎት ታሪፉ መሻሻል እንደሚገባው አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ የአቪዬሽን አገልግሎትን ለማዘመን ብዙ ሥራ መሠራት እንደሚኖርበትና ለዚህም የሠለጠነ የሰው ኃይልና ዘመናዊ መሣርያና ቴክኖሎጂ መስፋፋት እንደሚኖርበት አጽንዖት ሰጥተዋል፡፡

አቶ ፈጠነ ተሾመ በዐውደ-ጥናቱ ማጠቃለያ ላይ እንደገለጹት ያሉትን ችግሮችም ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት በየጊዜው በመገናኘት መፍታት እንደሚኖርባቸው አመልክተው፣ ኤጀንሲው ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ከማስፋት አኳያ አመርታዊ ለውጥ በማምጣት ላይ መሆኑንና የሠለጠነ የሰው ኃይልንም ከማጎልበት አኳያ በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር የረጅምና የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን በመስጠት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በዚሁ የግማሽ ቀን ዐውደ-ጥናት ላይ የግልና የመንግሥት የአየር ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ ባለ ድርሻ አካላትና የክልል የሚቲዎሮሎጂ ማዕከላት ኃላፊዎች መገኘታቸው ታውቋል፡፡





